# ዶር አብይ አህመድ ቦካሳን ቦካሳን ሸተተኝ!

ግንቦት 9ቀን 2010ዓም (16-05-20180)

አልበደል ቦካሳ መካከለኛዋ አፍሪካ በምትባለዋ የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት የነበረች አገር በፈረንሳይ ወታደራዊ ተቋም የሃምሳ አለቅነት ሹመት የነበረው፣በትምህርቱ ከሶስተኛ ክፍል ያላለፈ ሰው ሲሆን ፈረንሳዮች በኩዴታ ስልጣን ላይ ያወጡት አምባ ገነን  ነበር።በዚህም አልቆመም፣ በፈረንዮቹ ትብብር እራሱን ንጉስ ብሎ የንግሥና ስሙንም ናፖሊዎን ብሎ ዘውድ ለመጫን በቃ።ዘውድ ከመጫኑ በፊት ንጉስ እንደሚሆን የተነገረ ትንቢት ስለመኖሩ በማስነገር አንድ ቀን ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ አይቀርምና በሚል ስብከት ለመንገሥ ዝግጅት ያደርግ ነበር።ያልታደለው የመካከለኛው አፍሪካ ሕዝብም ለመቃወምም ሆነ ለመጠየቅ የማይችልበት ሁኔታ ላይ ስለነበር አንዳንዱ በእብደት ሌላውም የእግዚአብሔር ፈቃድ አድርጎ በመመልከት በዝምታ ዘውድ እንዲጭን አመቻቸለት።በፈረንሳዮች ተባባሪነት ናፖሊዎን ሁለተኛ ተብሎ ከአስር ኪሎ ያላነሰ በወርቅና አልማዝ የተንቆጠቆጠ ዘውድ አናቱ ላይ ደፋ።ይህ አምባገነን በራዲዮ ንግግር ሲያደርግ ተቀምጦ ማዳመጥ ያስቀጣ ነበር፤ሁሉም ንግግሩን ጀምሮ እስኪጨርስ ድረስ ቆሞ ፣ትንፋሽ ሳይተነፍስ የማዳመጥና ሲጨርስም አጨብጭቦ መሬት የመሳም ግዴታ ነበረበት።በዚህ ያይነቱ የእብደት ዘመኑ ፈረንሳዮች ከጎኑ በመቆም የግፉ ተባባሪዎች ነበሩ።ምን ቸገራቸው አውሮፓውያን የሚፈልጉትን እስካገኙ ድረስ የአፍሪካ ሕዝብ ኖረ አልኖረ ደንታቸው አይደለም።አሁንም ቢሆን ።

ከተወሰነ ዓመት በኋላ ሁኔታው እዬተለወጠ ሲመጣ፣የቦካሳ አቅም ሲዳከም፣ ፈረንሳዮች ጥቅማቸው አደጋ ውስጥ ሊገባ ሲል፣ ሆ ብለው የሰቀሉትን ቦካሳን አውርደው ለባለተረኛው አገልጋያቸው ስልጣኑን ሰጡት፤ ቦካሳም በስደት ሲንከራተት ኖሮ በመጨረሻው ላይ ምህረት ተደርጎለት አገሩ ገብቶ ትንሽ እንደቆዬ ሞተ። ከመሞቱ በፊት ግን ይኸው ጉደኛ ወደ ሌላ ትንቢት ውስጥ ገባና ዳግማዊ ክርስቶስ ነኝ ማለት ጀምሮ ነበር።መጨረሻው አላማረም እንደ ክርስቶስ በአህዛብ ተሰቅሎ ሳይሆን በካንሰር በሽታ ሞተ።

ይህንን ታሪክ ያነሳሁት ያለምክንያት አይደለም፤ በዘመናችን በአፍሪካ ምድር የዚህ አይነቱ የስልጣን አባዜ ያሳበዳቸው  በተደጋጋሚ ሲነሱ  በመታዬቱ ነው። የኡጋንዳውም አምባ ገነን ኢዲ አሚን ዳዳ እንዲሁ ዘውድ ያልጫነ ንጉስ ነበር።ሌሎቹም በስልጣን ያበዱ ዘውድ ባይጭኑም ዘውድ ያለበት ወንበር ላይ እንደተቀመጡ እሩቅ ሳንሄድ የራሳችንን ጉድ መንግስቱ ሃ/ማርያምን ማስታወስ ይቻላል።

አሁን ደግሞ ይባስ ብሎ አዲስ ንጉስ ነኝ ባይ በአገራችን ብቅ ብሏል።ይህንን  አስቂኝና አሳፋሪ ምኞት የሚነግረን የአሁኑ የኢሕአዴግ ሊቀመንበርና  ጠ/ሚኒስትር አብይ አህመድ ነው።አብይ እንደ  ባለ ትንቢተኛው ንጉስ አልበደል ቦካሳ ባለትንቢት ንጉስ ነኝ በማለት አፉን ሞልቶ ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ ለመንገሥ ሲዳዳው  ለመስማት በቅተናል። ጨዋታውን ወይም ቀልዱን የጀመረው እንዲህ በማለት ነው። ገና የሰባት ዓመት ልጅ በነበረበት ጊዜ ወላጅ እናቱ ንጉስ እንደሚሆን ይነግሩት እንደነበረና ያም ትንቢት አሁን የደረሰ መሆኑን በልበ ሙልነት ገልጾታል።መቼም የሁሉም ልጅ እናት ልጇን ከሁሉም በላይ አድርጋ ማሰብና መመኘት ለአብይ እናት ብቻ የተሰጠ ብቼኛ ምኞት አይደለም፤የሁሉም እናቶች ምኞት ነው። ይህንን የጋራ ምኞት አብይ ሆዬ አሁን ላለበት ስልጣን ማጠንከሪያ ለወደፊቱም ምኞቱ መንደርደሪያ አድርጎታል።የሚገርመው ደግሞ እንኳንስ ንጉስነትን ኢትዮጵያዊነትን የማያከብርና የማያውቅ የኢሕአዴግ የተባለው ድርጅት አባል ሆኖ ለሁሉም አባላት ለሳሞራና ለመለስም ሳይቀር   ይህንን ትንቢት እነግራቸው ነበር በማለት ፍላጎቱን የቆዬ ትንቢት አድርጎ ለማቅረብ መሞከሩ ነው።ጻረ ንግስና የሆኑትም እነመለስ

ዜናዊ ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ ይሁን ብለው የተቀበሉት ለማስመሰል ሞክሯል። እራሱንም ከአጼ ቴዎድሮስ ወዲህ ካሉት ነገስታት ውስጥ ጨምሮ ሰባተኛው የኢትዮጵያ ንጉስ አድርጎ አስቀምጦታል።ቅደም ተከተሉ እንደሚከተለው ነው።

አጼ ቴዎድሮስ፣አጼ ዩሃንስ፣አጼ ምንሊክ፣ልጅ እያሱ፣ንግስት ዘውዲቱ፣አጼ ሃይለሥላሴ፣ አጼ(ንጉስ)አብይ አህመድ(የንግስና ስሙ ወደፊት ዘውድ ሲጭን የሚታወቅ ይሆናል።

ኮሎኔል አብይ አህመድ በንጉስነት ፍላጎት ልክፍት ብቻ ሳይሆን በወታደርነት ሙያተኛነትም ምንም እንኳን የሹመት ልዩነት ቢኖረውም ከአልበደል ቦካሳ ጋር ምስስል አለው።ሌላው የባህሪ ምስስል ደግሞ በሚቀጥሉት ሳምንታት ወይም ወራቶች በገሃድ የሚታዩ ይሆናል።እኔ በበኩሌ ምንም ቢሆን ግን ከሚወክለው ኢሕአዴግ ከተባለ አገር አጥፊ ቡድን ጋር አብሮ ከከስልጣን እንዲወገድ እፈልግ ይሆናል እንጂ እንደ አልበደል ቦካሳ በስደት ሲንከራተት ይኑር የሚል ጨካኝ አንጀት የለኝም።ከመሰሎቹ ከኢሕአዴግ ባለስልጣኖች ጋር በአገሩ ላይ በሕግ ፊት ቀርቦ የሚያገኘውን አገኝቶ ይኑር ባይ ነኝ።

በዚህ የመንደርደሪያ የንጉስነት ፍላጎቱና ትንቢቱ ዶር/ኮሎኔል አብይ አህመድ ቦካሳን ቦካሳን ሸቶኛል። እንደቦካሳ የመከራ ዘመን እንዳያሰፍርብን ከአሁኑ መላ እናብጅለት።ለለውጥ የመጣና፣ለኢትዮጵያ አንድነት የቆመ አድርገው የሚያዩና የሚያጨበጭቡ፣ ነገ ደግሞ ህልምና "ትንቢቱ" ቢሳካለት ለንግሡ በዓሉ ሽር ጉድ ሲሉ ለማዬት እንችል ይሆናል፤የዛ ሰዎች ይበለን! ታላቁ ንጉሰ ነገስት ብለው መሬት ሲስሙ ባላየውም ሳስበው አዘንኩላቸው።

በተቃዋሚ ጎራ የተሰለፉት ድርጅቶችና ግለሰቦች እስከ አሁን ድረስ ሲታገሉ የኖሩት የኢሕአዴግ መስራችና አባል የሆነውን አንድ ድርጅት ህወሃትን ብቻ መሆኑን የአሁኑ አቋማቸው በግልጽ ያሳያል። ኢሕአዴግ የተባለው አገር አጥፊ ቡድንና የዘረጋው የጎሳ ስርዓት አልተነሳም።የተደረገው የባለስልጣኖች የቦታ መለዋወጥ ነው።ለውጡ የአንድ ጎሳ ድርጅት የሆነው የኦሕዴድ የበላይነት እንጂ ብሩህ ተስፋ የያዘ ለውጥ አልታዬም ። ተቃዋሚ ነን ባዮቹ የሚታገሉት ለስርዓት ለውጥ ሳይሆን ለባለስልጣኖች የቦታ መቀያዬር እንደነበረ በገሃድ ታይቷል። አሁን ለውጥ መጥቷል በሚል ሽፋን የስርዓቱ መሰረት የሆነውን፣ የኢትዮጵያን መበታተን የሚያበስረውን "ሕገ መንግሥት" ተቀብለው ለመግባት እየተሽቀዳደሙ ይገኛሉ። የኢትዮጵያን መገነጣጠል የሚፈልጉትና ቀደም ሲልም ይህንኑ መመሪያ የነደፉት የኦነግ አባላት ተንደርድረው በመግባት የመጀመሪያዎቹ ሆነዋል።ሌሎቹም ለመከተል በዝግጅት ላይ ናቸው።

ተቃዋሚን ማወቅና መቀበል ማለት ሕገ መንግሥቱንም የማይቀበለውንና የሚቃወመውን ማስተናገድ እንጂ የስርአቱን መመሪያና አገር አፍራሽ ሕዝብ አጫራሽ የሆነውን ሕገመንግሥት የሚቀበሉትን ብቻ ማስተናገድ አይደለም።እንደዚያ ከሆነ ተቃዋሚን ሳይሆን አማካሪዎችን መሰብሰብ ይሆናል።በዚህ መልኩ የሚገቡትም ተቃዋሚ ነን ብለው ሊመጻደቁ አይገባቸውም።በምክር ቤት በምርጫ የተወሰነ መቀመጫ አግኝተን እናማክራለን በሚል ተስፋ የትግሉን ጎራ ለመናድ የተነሱ ከመሆን በስተቀር ለመሰረታዊ ለውጥ ሊቆሙ አይችሉም።ለመሰረታዊ ለውጥ የሚታገለው በጥገና ለውጥ ሽፋን ትጥቁን ሊፈታ አይገባውም። የስርአቱን መሰረት የሆነውን ሕገ መንግሥት መቃወም የመጀመሪያው የትግሉ መነሻ ሊሆን ይገባል።

አገሬ አዲስ